ፍኖተ ዴሞክራሲ የኢትዮጵያ አንድነት ድምፅ

Finote Democracy Voice of Ethiopian Unity

efdpu@aol.com www. Finote.org

**ፕሮግራም**:- ረቡዕና እሁድ ከምሽቱ ሁለት ሰዓት እስከ ሶስት ሰዓት በ 13 ሜትር ባንድ

**Program**: Wednesday and Sunday 8:00PM- 9:00 PM on 25 meter band.

# <u>ዜና ዘገባ</u>

**ግንቦት 6 ቀን 2003 ዓ.ም**

**ወያኔ ያወጣውን አዲስ የታክሲ ስምሪት በመቃወም የስራ ማቆም አድማ ተደረገ፤**

**በህዝቡ ላይ ሌላ የታሪፍ ጫና ሊጫንበት መሆኑ ተጠቆመ፤**

**የነዳጅ አቅርቦት ስለሌለ ህዝቡ ተቸግሮዋል፤**

**ቤተ መንግስት ከወትሮው በተለየ ጥበቃው ተጠናክሮዋል፤**

ወያኔ እራሱ የፈጠራቸውን ችግሮች መልሶ እያባባሰ ህዝቡን ለከፋ ችግር እየዳረገ ባለበት በዚህ አጣብቂኝ ወቅት ሰሞኑንም የታክሲ ስምሪት መስመር አስተክላለሁ በሚል የባሰ በማበላሸቱ ችግሩ እጅግ በጣም የከፋ ደረጃ ላይ መድረሱ ታወቀ::

ከግንቦት 3 ቀን 2003 ዓ.ም ጀምሮ ታፔላ ለጥፈው ወደ ተሰጣቸው መስመር ብቻ እንዲሰሩ በማስገደዱ የታክሲ ባለንብረቶች እና ሹፌሮች በመተባበር የስራ ማቆም አድማ በማድረጋቸው የትራንስፖርት እጥረት ተከስቶ እንደዋለ ተዘዋዋሪ ዘጋቢያችን ገልፆዋል::

ወያኔ በፈጠረው ችግር የተነሳ የትራንስፖርት እጥረት በማጋጠሙ ህዝቡ ለከፋ ችግር ተዳርጎ ከረቡዕ ግንቦት 3 ቀን 2003 ዓ.ም ጀምሮ እስከ ዛሬ ድረስ ሊስተካከል ባለመቻሉ በአዲስ አበባ ከተማ የትራንስፖርት ችግሩ ከመቼውም ግዜ በላይ ውጥረት ውስጥ መግባቱ ታውቆዋል::

ያለ በቂ ጥናት እና የነፃ ገበያን መርህ በመጻረር የታክሲ ባለቤቶችን በማስገደዱ ብዙዎቹ የታክሲ ባለቤቶች ታፔላ ለጥፌ አልሰራም በሚያዋጣኝ መስመር መስራት መብቴ ነው በማለት ከፊሎቹ የስራ ማቆም አድማ በማድረጋቸው እና የተሰጣቸው ስምሪት ፍትሀዊ ካለመሆኑ ጋር ተደማምሮ የትራንስፖርት ችግሩ እጅግ አስቸጋሪ ደረጃ ላይ እንደሚገኝ ተዘዋውሮ ከተመለከተው ዘጋቢያችን ለመረዳት ተችሎዋል::

ዋና ዋና ተብለው የሚታወቁት ሰፈሮች ጭምር ወትሮ ተገልጋዩ በፈለገው ግዜ ሊያገኝ የሚችላቸውን ታክሲዎች ከረቡዕ ግንቦት 3 ቀን 2003 ዓ.ም ጀምሮ ወያኔ ባወጣው የታክሲ ስምሪት ባለንብረቶች ብሎም ሹፌሮች ከወያኔ ጋር ባለመስማማታቸው ከግማሽ በላይ የሚሆኑት ታክሲዎቻቸውን በጋራዥች እና በየሰፈሩ ብሎም በየአደባባዩ በማቆቸው የትራንስፖርት እጥረቱ ከመከሰቱም በላይ ከተማዋ ጭር ብላ እንደሰነበተች ለማየት ተችሎዋል::

ወያኔ በ1997 ዓ.ም የደረሰበትን ከፍተኛ ኪሳራ ለማካካስ ብሎም ቂሙን ለመወጣት ሲል የነደፈውን የማጥቃት እና ጨርሶ የማጥፋት ዘመቻ እያስፋፋ በመምጣት በለጋሽ ድርጅቶች የጀመረውን ጥቃት በነጋዴዎች አቀጣጥሎ ዛሬ ደግሞ የታክሲ ባለንብረቶችን ጨርሶ ባሪያ ለማድረግ ስምሪት ብሎ መቆጣጠሪያ መመሪያ ቢያወጣም እስከ ዛሬ ድረስ ከግማሽ በላይ የሆኑት የስራ ማቆም አድማ አድርገው እንደሚገኙ ታውቆዋል::

በተለይ ረቡዕ ዕለት የታክሲ እጥረት መከሰቱን የተረዱት ቁጥራቸው የበዛ የመንግስት መስሪያ ቤት ሰራተኞች በተፈጠረው ችግር በመበሳጨት ወያኔን እያማረሩ ወደ የቤታቸው የተመለሱ ሲሆን ሌሎቹም የግል ድርጅት ሰራተኞች በእግራቸው ብዙ ኪሎ ሜትሮችን ለመጉዋዝ መገደዳቸውን ተዘዋዋሪ ዘጋቢያችን ያስተዋለውን ገልፆዋል::

በየጊዜው የማስተካከያ እርምጃ እወስዳለሁ እያለ ያለ አንዳች በቂ ጥናት ህዝቡን ለከፋ ችግር እየዳረገ የሚገኘው የወያኔ ቡድን ከዚህ ቀደም ጅምላ አከፋፋይ ከነበሩት ላይ የንግድ ፍቃዳቸውን ነጥቆ በራሱ በሚቆጣጠረው ጅንአድ በኩል ዘይትና ስኩዋር አቀርባለሁ ብሎ ቢጀምርም ሊሳካለት ያልቻለ ከመሆኑም በላይ እጅግ ከባድ ችግር ተፈጥሮ ሊስተካከል ከማይችልበት ደረጃ ላይ መድረሱ በገሀድ እየታየ ሲሆን ዛሬ የአንድ ሊትር ዘይት ዋጋ 60 ብር ፤የአንድ ኪሎ ስኩዋር ዋጋ 26 ብር ቀድሞ 6 ብር ሲሸጥ የነበረው ሳሙና በይፋ 9 ብር እየተሸጠ ቢገኝም ወያኔ የዋጋውን ንረት እያባባሰ ሊቆጣጠረው ያልቻለበት ደረጃ ላይ መድረሱም ታውቆዋል::

በ1997 ዓ.ም በተደረገው ሀገር አቀፍ ምርጫ በዝረራ በመሸነፉ ደንግጦ እስከ አሁን ወደ ልቦናው ያልተመለሰው የወያኔ ቡድን የራሱን ጥላ ሲያይ እየደነበረ በየግዜው በሚወስዳቸው እርምጃዎች ሀገሪቱን ወደ መቀመቅ እየከተተ...... ህዝቡዋን ለችግር እየዳረገ ከመሆኑም በላይ በተለይ በነጋዴዎች ላይ በያዘው ቂም ቀስ በቀስ እየገዘገዘ ከጫወታ ውጭ እያደረጋቸው መገኘቱን በሚወስዳቸው እርምጃዎች እያሳየ መሆኑን ነጋዴዎች በምሬት ሲገልፁም ተደምጦዋል::

ባለሀብቶችን ለተቃዋሚ ፓርቲዎች ድጋፍ ስትሰጡ ነበር በሚል አንዱን በአራጣ ....ሌላውን በመሬት ስርቆት..... እንዲያም ሲል በሻት ሰበብ እየወነጀለና ሀሰተኛ ታፔላ እየለጠፈ ወደ እስር ቤት እየከተታቸው ከመሆኑም በላይ በቅጣት ሰበብ ለዘመናት ያፈሩትን ሀብት እየወረሰ መገኘቱ ስርዓቱ የህዝብ ድጋፍ የሌለው ከመሆኑ ጋር ተዳምሮ እራሱ የሚፈጥረው ችግር መሆኑንም ባለሀብቶች እየተናገሩ ይገኛሉ::

የመንግስት ሰራተኛውን ጭምር በቁጥጥር ስር ለማዋል በየግዜው የተለያየ መመሪያና ደንብ እያወጣ እያንገላታው ያለው የወያኔ ቡድን ከእለት ጉርሱ ቀንሶ ለልጆቹ ማስተማሪያ እንዳይተርፈው

የተለያዩ ሰበቦችን እየነደፈ በግዴታ መዋጮ እያለ እያሰቃየው ሲሆን ህዝቡም ስለ ኑሮው እንጂ ስለ ሌላ ነገር እንዳያስብ በነዳጅ ላይ እየቆለለ የእህልና ጥራጥሬ ዋጋ እንዲያሻቅብ አድርጎ እየተጫወተብን ይገኛል ያሉት የአዲስ አበባ ነዋሪዎች ይሄ ሁሉ ግፍ እና መከራ አልበቃ ብሎት ሰሞኑን ደግሞ ያለ አንዳች በቂ ጥናት እና ዝግጅት ብሎም በቂ የመኪና አቅርቦት በሌለበት ድንገት የታክሲ ስምሪት ብሎ መጀመሩ ህዝቡን ከመናቁም በላይ ምን ያመጣል በሚል በልበ ድፍንነት የወሰደው እርምጃ መሆኑን ያሳያል ሲሉም በብስጭት ይገልፃሉ::

ከዚህ ቀደም ህዝቡ ረዥም መንገዶች ወጥ በሆነ መልኩ ሲጉዋዝበት የነበረውን በአዲሱ የታክሲ ስምሪት ሁለት እና ከዚያም በላይ ታክሲዎችን ለመያዝ የሚገደድ ከመሆኑም በላይ ተሳፋሪ የሚበዛበት ሰፈር መኪና አሳንሶ  ተሳፋሪ በሌለበት ሰፈር ደግሞ መኪኖችን በብዛት መድቦ ታክሲዎቹ ቀኑን ሙሉ ስራ ፈትተው እንዲውሉ ከማድረጉም ባሻገር በየቦታው ላይ እስከ ዛሬ ሲያስተናብሩ የነበሩትን ተራ አስከባሪዎች አባርሮ የወያኔ ወጣት ፎረም አባሎች እንዲቆጣጠሩት ማድረጉንም ለማወቅ ተችሎዋል::

ወያኔ ባደረበት ፍርሀት የተነሳ በየግዜው በሚወስዳቸው የህዝብ ተፃራሪ እርምጃዎች  ህዝቡ ለእንግልት እና ለስቃይ እየተዳረገ ቢሆንም ከማሻሻል ይልቅ ችግሩ እንዲባባስ እያደረገ ሲሆን አሁንም የታክሲ ስምሪት ብሎ ባወጣው እቅድ ህዝቡ ለከፍተኛ ችግር ተዳርጎ ሰራተኛው ሰዓታት እያረፈደ...... ተማሪው ትምህርቱን እያቋዋረጠ .....ህዝቡም ከቦታ ወደ ቦታ እንዳይንቀሳቀስ ማነቆ የፈጠረ መሆኑም ታውቆዋል::

ሌላው ቢቀር እስከ ዛሬ ከ10 ዓመት በላይ የታክሲ አስከባሪ ሆነው የሰሩትን ወጣቶች አባርሮ የፎረም አባሎችን እንዲቆጣጠሩ በማድረጉ የተነሳ ወጣቱ እርስ በርስ እንዲጋጨና ጥላቻ በመሀላቸው እንዲነግስ ያደረገ ከመሆኑም በላይ ለዓመታት በዚሁ ስራ ላይ ያሉትንና ቤተሰብ መስርተው ልጆች ወልደው በመኖር ላይ ያሉትን ዜጎች አፈናቅሎ ለፎረም  አባሎች ቦታውን በመስጠቱ  ሰሞኑን በየቦታው ከፍተኛ ግጭት እና ትርምስ ተቀስቅሶ ብዙ ወጣቶች ጉዳት እንደደረሰባቸው ለማወቅ ተችሎዋል::

ነባር የታክሲ አስከባሪዎች በየክፍለ ከተማው  አስተዳደሮች እየገቡ ለብዙ ዓመታት በስራው ላይ መኖራችንን እያወቃችሁ እኛን አባርራችሁ የፎረም አባሎችን ማስገባታችሁ ተገቢ ካለመሆኑም በተጨማሪ የዜግነት ሰርቶ መኖር መብታችንን ገፍፋችሁዋል ብለው ጥያቄ ቢያቀርቡም እናንተም  እንደነሱ የፓርቲውን መመሪያና ደንብ ተቀብላችሁ አባል መሆን ይጠበቅባችሁዋል ሲሉ ምላሽ የሠጡዋቸው ቢሆንም ተራ አስከባሪ የነበሩት ወጣቶች በበኩላቸው በርሀብ እናልቃለን እንጂ የወያኔ አባል አንሆንም በማለት ምላሽ እንደሰጡዋቸው ተደምጦዋል::

በአሁኑ ሰዓት በአዲስ አበባ ከተማ በግብታዊነት የተጀመረውን የታክሲ ስምሪት በመቃወም ብዙዎቹ ባለንብረቶች የስራ ማቆም አድማ አድርገው እስከ ዛሬዋ ዕለት ድረስ ስራ ያልጀመሩ መሆኑንም ከደረሰን ዘገባ ለማወቅ ተችሎዋል::

የስራ ማቆም አድማ ያደረጉትን የታክሲ ባለንብረቶች እና ሹፌሮች ወደ ስራ ለማስገባት ሲባል ህዝቡን (ተሳፋሪውን) ያላገናዘበ አዲስ የታሪፍ ጭማሪ ሊደረግላቸው የታቀደ መሆኑንም ከመንገድ ትራንስፖርት ቢሮ ሾልኮ የደረሰን ጥቆማ አጋልጦዋል፡፡

በየወሩ በሚደረገው የነዳጅ ጭማሪን ተከትሎ በየግዜው ትራንስፖርት ታሪፉ እያሻቀበ መጥቶ ቀድሞ 55 ሳንቲም የነበረው አጭር ጉዞ በእጥፍ ጨምሮ ዛሬ 1ብር ከ25 ሳንቲም የደረሰ ሲሆን አሁን ደግሞ ለታክሲዎች ሲባል ብቻ አዲስ ታሪፍ ተብሎ በህዝቡ ላይ ሊጫንበት መሆኑን ከውስጥ አዋቂ ምንጮች የደረሰን ጥቆማ ገልፆዋል፡፡

ይህ በእንዲህ እንዳለ ወርሀዊ የነዳጅ ጭማሪ ይደረጋል በሚል ስጋት ሰሞኑን በየነዳጅ ማደያው መኪኖች እየተሰለፉ መጨናነቅ መፈጠሩ ታወቀ፡፡

ያልተጣራና ንፁህ ቤንዚን ያልሆነ ነዳጅ ከኢታኖል ጋር እየደባለቀ የሚሸጠው ወያኔ እሱንም በአግባቡ ማቅረብ አቅቶት  እጥረት በመፈጠሩ ነዳጅ የለም እየተባሉ በየነዳጅ ማደያው ባለመኪናዎች ተሰልፈው ለመዋል መገደዳቸው ታውቆዋል፡፡

የደሀው ህዝብ ማብሰያ የሆነው ጋዝም በመጥፋቱ ህዝቡ ጠዋት ወጥቶ ማታ ባዶ እጁን እየተመለሰ ሲሆን ክፍለ ሀገር ለስራ የወጡ መኪኖች በነዳጅ እጦት ለቀናት በየመንገዱ  ቆመው ለመሰንበት እንደተገደዱም ለማወቅ ተችሎዋል፡፡

ኢታኖልና ቤንዚን እየደባለቀ የሚሸጠው የወያኔ ቡድን የዓለም የነዳጅ ዋጋ ቢቀንስም እሱ እየጨመረ ስንጥቅ ትርፍ ከህዝቡ ላይ እያግበሰበሰ ከመሆኑም ሌላ በቂ አቅርቦት ስለሌለው ህዝቡ በዚህም እየተጎዳ መሆኑ ታውቆዋል፡፡

ዛሬ የአንድ ሊትር ቤንዚን ዋጋ 21 ብር የደረሰ ሲሆን የናፍጣ ዋጋውም 18 ብር ደርሶ የቤት መጠቀሚያ ጋዝም 14 ብር አሻቅቦ ህዝቡ ከመግዛት አቅሙ በላይ እየሆነበት ባለበት በዚህ ግዜ በየነዳጅ ማደያው የቤት ውስጥ ማብሰያ ጋዝ በቂ አቅርቦት ስለሌለ ብቻ ጠዋት ወጥተው ማታ ባዶ እጃቸውን የሚመለሱ ዜጎች ቁጥራቸው ብዙ መሆኑ ይታወቃል፡፡ይህንን ችግር በአግባቡ መቅረፍ ያልቻለው ወያኔ የህዝቡን ስቃይ ለማባባስ ሲል ብቻ የታክሲ ስምሪት መጀመሩ የህዝቡን ችግር ያላገናዘበ ዘለቄታነት የሌለው መሆኑን ያሳያል ሲሉም ነዋሪዎች በምሬት ይገልፃሉ፡፡

ለብዙ ዓመታት በውጭ ሀገር ኖረው የመጡ ኢትዮጵያውያኖች ዘመዶቻቸውን ለመጠየቅ ወደ ክፍለ ሀገር ሄደው ለመመለስ በነዳጅ አጥረት ምክንያት ሲሰቃዩ ማስተዋል የእለት ተዕለት እንቅስቃሴ ነው ያሉት ሹፌሮች  ሰፊ ስራ ሊሰራባቸው የሚገቡ ጉዳዮች እያሉ በቂ የመኪና አቅርቦት በሌለበት በአዲስ አበባ ከተማ አዲስ የታክሲ ስምሪት ማውጣቱ የሚያሳፍር ብቻ ሳይሆን ሆን ተብሎ ህዝቡን ለማሰቃየት የተደረገ ነው ሲሉም በብስጭት ይገልፃሉ፡፡

በሌላ ዜና ከመስከረም ወር ጀምሮ በወያኔ ቡድን ውስጥ በተከሰተ ውስጣዊ ሽኩቻ የተነሳ የወያኔው መሪ መለስ ዜናዊ በፍርሀት ውስጥ መሆኑን የሚያሳዩ ፍንጮች ከቤተ መንግስት እየታዩ መሆኑ ተጠቆመ፡፡

በወያኔ ቡድን ውስጥ በተከሰተ ውስጣዊ ሽኩቻ የተነሳ ሲታመሱ ከሰነበቱ በሁዋላ ብዙ የኦህዴድ ካድሬዎችን ለእስር ዳርጎ ጥቂት ማስተንፈስ የቻለ ቢሆንም ከውጭም የአረብ ሀገራት ብሎም የሰሜን የአፍሪካ ሀገራት ህዝቦች በዲሞክራሲ እጦትና በኑሮ ውድነት ሳቢያ በተቀሰቀሰ አመፅ ሲያምሳቸው በመክረሙ በመደናገጥ የደህንነት መዋቅሩን እጅግ በጠነከረ ሁኔታ ከማሰማራቱ በተጨማሪ የቤተ መንግስት ዙሪያ ጥበቃውም ከመቼውም ግዜ ላይ ተጠናክሮ እየተጠበቀ መሆኑ ተጠቁሞዋል::

በተለይ ሰሞኑን ከወትሮው በተለየ ሁኔታና እስከ አሁን ድረስ ታይቶ ባልታወቀ ሁኔታ የቤተ መንግስት ዙሪያ ጥበቃ ኮማንዶ በሰለጠኑ የፌዴራል ፖሊስ ተወርዋሪ ፖሊሶች በእግርና በፓትሮል ተወጥሮ የሚገኝ ሲሆን ፖሊሶቹ ጥይት የማይበሳው ልብስ እንዲለብሱ መደረጉንም በአይን ለማየት ተችሎዋል::

መለስ ዜናዊ በራሱ ሰዎች ላይ ጭምር እምነት የሌለው በመሆኑ ፍርሀቱ እያየለ በመምጣቱ በቤተ መንግስት ግቢ ውስጥ ከአራት ዙር በላይ ዙሪያ ቀለበት ጥበቃ ያሰማራ ከመሆኑም በተጨማሪ ከግቢ ውጭ በጥበቃ ላይ ከተመደቡት የመከላከያ አባሎች በተጨማሪ ልዩ ኮማንዶ ሰለጠኑ የተባሉትን የፌዴራል ፖሊስ ተወርዋሪ ፖሊሶች ማሰማራቱም የፍርሀቱ መናርን የሚያሳይ ነው ተብሎዋል::

አራት ዙር ቤተ መንግስት ዙሪያ ጥበቃ ከሚያደርጉት ኮማንዶዎች በተጨማሪ ከግቢ ውጭ የተመረጡ የፌዴራል ተወርዋሪ ፖሊሶች ጥይት የማይበሳው ልብስ ለብሰው በፓትሮል መጠበቅ የጀመሩ ሲሆን በቤተ መንግስት ዙሪያ የሚጉዋዙ ሰዎችን በማስፈራራትና በመገላመጥ እያስደነገጡዋቸው መሆኑንም በቦታው የተገኙ ሰዎች አረጋግጠዋል::

ቅጠልያ ቀለም ያለው ጥይት የማይበሳው ልብስ የለበሱት የፌዴራል ፖሊስ ተወርዋሪዎች በአራት ኪሎ ቤተ መንግስት ዙሪያ እየተሽከረከሩ ህዝቡንም እያስፈራሩ ከመሆኑም በላይ እነሱም ፋታ አጥተው ከወዲያ ወዲህ ሲመላለሱ የሚውሉ ሲሆን ለቤተ መንግስት ጥበቃ ሁለት ጄኔራሎችም እንደተመደቡ ከመከላከያ የተገኘው ጥቆማ አብራርቶዋል::

የጅቡቲው ፕሬዝዳንት በዓለ ሲመት ላይ ለመገኘት እና ወደ ቱርክ ስብሰባ በሔደበት ወቅት ሁለቱ ጄኔራሎች ቤተ መንግስቱን እንዲቆጣጠሩ የተመደቡ ሲሆን በበላይነት ጄኔራል ሳሞራ የኑስ እንደሚመራውም የመከላከያ ውስጥ አዋቂ ምንጮች ጠቁመዋል::

የራሱን ሰዎች ጭምር እየፈራና እየተጠራጠረ የመጣው የወያኔ ቡድን መሪ መለስ ዜናዊ በተለይ ከቅርብ ግዜ ወዲህ ያመጣው የተለየ ባህሪ በቢሮው ውስጥ ጭምር ባለስልጣናት ሲገቡ ሲሉ ጥብቅ ፍተሻ እንዲደረግላቸው የታዘዘ ሲሆን አንዳንዶች በሚደረግባቸው ጥብቅ ፍተሻ በመደናገጥ ጫማዎቻቸውን አውልቀው በካልሲ እስከመግባት እንደሚደርሱም የቤተ መንግስት ምንጮች ጠቁመዋል::

ከሲቪል ባለስልጣናት ይልቅ የወታደራዊ ጄኔራሎችን በጣም እየቀረበ የመጣው መለስ ዜናዊ ችግር ቢፈጠር ሊያድኑኝ የሚችሉት እነሱ ናቸው በሚል መሆኑን የጠቆሙት ምንጮቹ ሰሞኑንም በመስጢር ከአራት ጄኔራሎች ጋር ብቻውን በምስጢር ቤተ መንግስት ውስጥ እንደተገናኘ ና እንደመከረ ምንጮቹ ጠቁመዋል::

ጀኔራል ሳሞራ የኑስ ፤ሌ/ጀኔራል ታደሰ ወረደ ፤ሜ /ጀ/ል ዮሀንስ ገብረ መስቀልና አንድ ለግዜው ስሙ ያልተጠቀሰ ጀኔራል በመሆን ለሁለት ተከታታይ ቀናት በቤተ መንግስት በሚገኘው መኖሪያ ቤቱ ውስጥ እየተገናኙ ሲወያዩ እንደነበር ምንጮቹ አጋልጠዋል፡፡